# እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!

## ማስታወቂያ

### የአርብ ፕሮግራም

በአርቡ ፕሮግራማችን ጌታ እየባረከን ነው። በልዩ ልይ ጉዳዮች ላይ እንጸልያለን፤ ቃሉን እንማራለን። የምትችሉ እንድትካፈሉ እናበረታታለን። ጌታ ይባርካችሁ!

### የገንዘብ ማሰባሰቢያ ቅጽ

ለሕንጻ ግዢ የገንዘብ ማሰባሰቢያ የተዘጋጀውን ቅጽ ሞልታችሁ ያልመለሳችሁ ወገኖች እባካችሁ ሞልታችሁ ለዲያቆናት ስጡልን። የህንጻ ኮሚቴ አስተባባሪዎች። እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

"ወደ ውጭም አውጥቶ:- ጌቶች ሆይ፥ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? አላቸው።
እነርሱም:- በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት።" (ሐዋ. 16፡ 30-31)

*"በሚመጣው ዘመን ያዕቆብ ሥር ይሰድዳል፥ እስራኤልም ያብባል ይጨበጭብማል፤ በፍሬያቸውም የዓለሙን ፊት ይሞላሉ።" (ኢሳ. 27፡6)*



- ⇒ የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ በምጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?
- ⇒ ማገልገል ይፈልጋሉ?
- ⇒ Yeec.org App ጭነዋል?
- ⇒ http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?

ሽማግሌዎችን ለማግኘት:-
773-886-0818 (ሲሳይ)
773-865-6102 (ብረሃኑ)
773-507-0194 (ጋሽ አያሌው)
773-910-0485 (ፒተር)
773-961-5332 (ጌቱ)


### መደበኛ ፕሮግራሞች

እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.
አርብ 7:00 p.m. -- 9:00 p.m.

# የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን

# Chicago Yemsrach Evangelical Church

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2፡10




"ጐለመስሁ አረጀሁም፤ ጻድቅ ሲጣል፥ ዘሩም እህል ሲለምን አላየሁም።"
(መዝ. 37፡25)

Chicago Yemsrach Evangelical Church
4455 N. Seeley Avenue
Chicago, IL 60625

### መደበኛ ፕሮግራሞች

እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.
አርብ 7:00 p.m. -- 9:00 p.m.

**October 15, 2017** | **ጥቅምት 5፤ 2010 ዓ.ም.**

## የእለቱ ፕሮግራም መርሃ-ግብር

| | |
|---|---|
| ጸሎት መሪ................. | ወንድም ሲሳይ መሸሻ |
| አምልኮ....................... | የቤተክርስቲያን አምልኮ ቡድን |
| ፕሮግራም መሪ .......... | ወንድም ሲሳይ መሸሻ |
| ቃል ............................ | ወንድም ረድኤቱ ካሳ |
| ማጠቃለያ ................. | ፕሮግራም መሪ |

### የሳምንቱ ጥቅስ

**“የእግዚአብሔር መንግሥት ጽድቅና ሰላም በመንፈስ ቅዱስም የሆነ ደስታ ናት እንጂ መብልና መጠጥ አይደለችም።”** (ሮሜ. 14፡17)

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች**

| መሪ | ቀን | አድራሻ |
|---|---|---|
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 6602 N. Damen Ave., Chicago IL 60626 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሐሙስ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| ወ/ም ሰለሞን ወመሳ | ቅዳሜ | 549 Sheridan Rd., Apt. 3, Evanston, IL 60202 |
| ወ/ም መስፍን ጌታቸው | ዕሮብ | 4631 N. Beacon St., Chicago, IL 60640 |

## መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

**ጸሎት አስተምረን -- መንግስትህ ትምጣ (ክፍል ስድስት)**

*“እርሱም በአንድ ስፍራ ይጸልይ ነበር፥ በጨረሰም ጊዜ ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ፦ ጌታ ሆይ፥ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርቱን እንዳስተማረ እንጸልይ ዘንድ አስተምረን አለው። አላቸውም፦ ስትጸልዩ እንዲህ በሉ፦ በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ... መንግስትህ ትምጣ ...” (ሉቃ. 11፡1-2)*

“መንግስትህ ትምጣ” ብለን ስንጸልይ የእግዚአብሔር ኃይልና ሕልውና በሕይወታችን፣ በቤተ ክርስቲያን እና በምንኖርበት አካባቢ እንዲገዛ መፍቀዳችን እንደሆነ አይተናል። የእግዚአብሔር መንግስት ከምንም በላይ የምንፈልጋት መሆን እንዳለበትም አይተናል። ዛሬ ደግም የእግዚአብሔርን መንግስት መፈለግ ምን ማለት እንደሆነ እናያለን።

ሐዋሪያው ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜ 14 ቁጥር 17 ላይ እንደገለጸት “የእግዚአብሔር መንግሥት ጽድቅና ሰላም በመንፈስ ቅዱስም የሆነ ደስታ ናት እንጂ መብልና መጠጥ አይደለችም።” በዚህ ክፍል የእግዚአብሔር መንግስት ምን እንደምትመስል ቃሉ ያስተምረናል። በመጀምሪያ አሉታዊውን ሃሳብ ብንመለከት የእግዚአብሔር መንግስት የመብልና የመጠጥ ጉዳይ አይደለችም። በክፍሉ አውድ ስንመለከተው የምንበላው ወይንም የምጠጣው ነገር እርስ-በርስ ካለን ግንኙነት አንጻር ፋይዳ ሊኖረው ይችል እንደሆነ እንጂ በራሱ በእግዚአብሔር መንግስት የምንመላለስበትን አቋም አያመለክትም። ሌሎችን የሚያሰናክል ነገር ማድረግ መልካም አይደለም ነገር ግን ወደ አፍ የሚገባው ጌታችን እንዳስተማረው የሚያረክስም፣ የሚቀድስም አይደለም። እርሱ በሆድ አልፎ በእዳሪ ይወጣል። ይልቁንም ከአፍ የሚወጣው ከልብ ይወጣልና ሰውን የሚያረክሰው ያ ነው። (ማቴ. 15፡ 11፣ 17፣ 18) በሌላ መልኩ ደግም የእግዚአብሔር መንግስት ጉዳይ ምድራዊ የሆነ የኑሮ መብልና መጠጥ ጉዳይ አይደለም። እርግጥ ነው መንግስቱንና ጽድቁን ስንፈልግ እግዚአብሔር ለኑሮ የሚያስፈልገንን ሁሉ አያሳጣንም። እንዲያውም ይጨምርልናል። (ማቴ. 6፡ 33) ንጉስ ዳዊትም “ጐለመስሁ አረጀሁም፤ ጻድቅ ሲጣል፥ ዘሩም እህል ሲለምን አላየሁም” ብሏል። በጎልምስና እና በእርጅና መካከል በትንሹ አርባ አመት አለ። ዳዊት የሕይወት ዘመን ተመክሮውን ሲካፍለን የሚለው ነገር እግዚአብሔርን የሚፈልግ ሰው ተጥሎ እንዳላየ ነው። የሚቀድመውን ካስቀደምን እግዚአብሔር መኖሪያችን ይሆንልናል።

በአውንታዊ መልኩ ደግም የእግዚብሔር መንግስት በሶስት ሃሳቦች ተገልጻለች። የእግዚአብሄር መንግስት አንደኛ የእግዚአብሔር ጽድቅ ናት። ሁለተኛ የእግዚአብሔር መንግስት የእግዚአብሔር ሰላም ናት። ሶስተኛ የእግዚአብሔር መንግስት በመንፈስ ቅዱስ የሚሆን ደስታ ናት። እንግዲህ የእግዚአብሔርን መንግስት ስንፈልግና መንግስትህ ትምጣ ስንል እየፈልግን ያለነው የግዚአብሔርን ጽድቅ፣ ሰላምና በመንፈስ ቅዱስ የሚሆንን ደስታ ነው። እነኚህን ሃሳቦች በዝርዝር በሚቀጥሉት ጽሑፎች እናያለን።